# የዲሲ የጤና አሊያንስ (DC Healthcare Alliance)

## መብትዎን ይወቁ!

Legal Aid Society OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

## የዲሲ የጤና አሊያንስ ምንድን ነው?



አሊያንሱ በዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና ሜዲኬድ ለሌላቸው ሰዎች **ነፃ** የጤና ኢንሹራንስ ይሰጣል። የሐኪም

ወይም የሆስፒታል ጉብኝቶች፣ የቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤ፣ የጥርስ አገልግሎቶች፣ የሚታዘዙ መድሐኒቶች፣ እና ብዙ ሌሎች አገልግሎቶችን ወጪ ይሸፍናል።

## አሊያንሱን ማግኘት እችላለሁኝ?

አሊያንሱን ማግኘት የሚችሉት እርስዎ፥

- ☐ **ዕድሜዎ 21 እና ከዛ በላይ** ከሆኑ
- ☐ **የዲሲ ነዋሪ** ከሆኑ
- ☐ **የጤና ኢንሹራንስ** የሌለዎት ከሆነ(ሜዲኬድ እና ሜዲኬር ጨምሮ)
- ☐ በጥሬ ገንዘብ ወይም የባንክ አካውንት ውስጥ ከ **$4,000 (ለግልሰቦች)** ወይም **$6,000 (2+ ሰዎች)** ያነሰ ገንዘብ ካላቹህ።
- ☐ **ዝቅተኛ ገቢ** ያለዎት ከሆነ። ከታች ያለውን ገበታ ምስል ይመልከቱ።

| የቤተሰብ ብዛት | አጠቃላይ ገቢዎ ከዚህ ያነሰ መሆን አለበት፦ |
|---|---|
| 1 | $2,146/በወር |
| 2 | $2,903 |
| 3 | $3,660 |
| 4 | $4,417 |
| 5 | $5,173 |
| 6 | $5,930 |
| 7 | $6,687 |
| 8 | $7,743 |

## እንግሊዘኛ በደንብ የማልናገር ከሆነ ማመልከት እችላለሁኝ?

**አዎ።** ሕግ የሚለው መንግስት በእርስዎ ቋንቋ ሊያግዞት ይገባል ነው። የሚፈልጉትን ኤጀንሲ በእርስዎ ቋንቋ እገዛ እንደሚሹ ይንገሯቸው።

## የአሜሪካ ዜግነት የለኝም። ማመልከት እችላለሁኝ?

**አዎ!** ብቁ የሆኑ ሁሉም የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች፣ **ምንም አይነት የኢሚግሬሽን አቋም ቢኖሮትም፣** አሊያንሱን ማግኘት ይችላሉ። ይሄ ወረቀት የሌላቸው ስደተኞችን ይጨምራል፦

*አንዳንድ ወረቀት ያገኙ ስደተኞች የግል ኢንሹራንስ ማግኘት ወይም የታክስ ቅጣት ማግኘት አለባቸው። የበለጠ ለማወቅ ሌጋል ኤድን ያግኙ።*

## አሊያንሱ ምን  ዓይነት አገልግሎቶችን ይሸፍናል?

አሊያንሱ ሊከፍል የሚችለው፦

- ለሐኪም ጉብኝቶች
- የመከላከያ ሕክምና (የጥንቃቄ ምርመራ፣ የአመጋገብ እና የተመጣጠነ ምግብ)
- የቅድመወሊድ ሕክምና (እርግዝና)
- በሐኪም የሚታዘዙ መድሐኒቶች
- የላብራቶሪ አገልግሎቶች
- የሕክምና አቅርቦቶች
- እስከ $1,000 ድረስ የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች

***አሊያንስ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ለማወቅ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይሂዱ***

**እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake/።

## አልያንስ ላይ እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

**አንድ ማመልከቻ ላይ** የምግብ ድጎማ፣ ታንፍ፣ ሜዲኬድ እና ዲሲ የሕክምና  አልያንስን ጨምሮ **ሁሉም** የሕዝብ ጥቅማጥቅሞች ላይ ማመልከት ይችላሉ።

**ቅደም ተከተል 1፡- የሚያስፈልጎትን ሰነዶች ያግኙ።** ኦርጅናሎቹን እንዳይልኩ! በፎቶ ያንሱት ወይም ኮፒ ያድርጓቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የእርስዎ የፎቶ መታወቂያ። | የእርስዎ የማህበራዊ ደህንነት ካርድ (ያለዎት (ያለዎት ከሆነ) | የገቢ ምንጭ ማሳያ ( ልክ ልክ እንደ የክፍያ ማረጋገጫ) | የመኖሪያ አድራሻ (ልክ (ልክ እንደ ክፍያ ደረሰኝ) ደረሰኝ) | በቤተሰብዎ ውስጥ ለሚኖሩ እያንዳንዱ ሰዎች ሰዎች የልደት ምስክር ወረቀቶች |

**ቅደም ተከተል 2፡- ከአራት መንገዶች ውስጥ በአንዱ ያመልክቱ፡-**

**በአካል በመገኘት** በእነዚህ **ESA አገልግሎት ማዕከሎች ውስጥ አንዱ ላይ።** በሚያመለክቱበት ሰዓት ማረጋገጫ ደረሰኝ ይጠይቁ።

- **አናኮስቲያ የአገልግሎት ማዕከል (Anacostia Service Center)**
  2100 Martin Luther King Jr. Avenue SE
  (202) 645-4614
- **ኮንግረስ ሃይትስ አገልግሎት ማዕከል (Congress Heights Service Center)**
  4001 South Capitol Street SW
  (202) 645-4546
- **ኤች ስትሪት አገልግሎት ማዕከል (H Street Service Center)**
  645 H Street NE
  (202) 698-4350
- ***[ተዘግቷል]* ፎርት ዴቪስ አገልግሎት ማዕከል (Fort Davis Service Center)**
  3851 Alabama Avenue SE
  (202) 645-4500
- ***[ተዘግቷል]* ታይለር ስትሪት አገልግሎት ማዕከል (Taylor Street Service Center)**
  1207 Taylor Street NW
  (202) 576-8000

**በስማርት ስልክዎ፡-** ኦንላይን የመተግበሪያ መደብር ላይ የ **District Direct** መተግበሪያን ያውርዱ። ስልክዎ ላይ ሆነው ያመልክቱ። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ።

**ኦንላይን፡-** ወደዚህ ይሂዱ https://districtdirect.dc.gov/ua/። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ። ያስረከቧቸውን ነገሮች ቅጂ

ያስቀምጡ።

**በአካል በመገኘት** በእነዚህ **ሆስፒታሎች ወይም የማህበረሰብ የጤና ክሊኒኮች ላይ ይሂዱ።**

- **ሆስፒታሎች፡-** ዩናይትድ ሜዲካል ሴንተር (United Medical Center)፣ የዋሽንግተን ሆስፒታል ሴንተር (Washington Hospital Center)፣ ፕሮቪደንስ ሆስፒታል (Providence Hospital)፣ ሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል (Howard University Hospital)
- **ኮንግረስ ሃይትስ ሐልዝ ሴንተር (Congress Heights Health Center)**
  3720 MLK Jr. Ave. SE, 20032
  (202) 279-1800
- **ሃንት ፕሌስ ኮሚኒቲ ሐልዝ ሴንተር (Hunt Place Community Health Center)**
  4130 Hunt Pl. NE, 20019
  (202) 388-8160
- **ላ ክሊኒካ ዴል ፑብሎ (La Clínica del Pueblo)**
  2831 15th St. NW, 20009
  (202) 462-4788
- **ለወሊድ እና የልጆች ሕክምና የሜሪ ማዕከል (Mary's Center for Maternal and Child Care)**
  2333 Ontario Rd. NW, 20009
  (202) 483-8196
- **ሰውዝዌስት ኮሚኒቲ ሐልዝ ሴንተር (Southwest Community Health Center)**
  850 Delaware Ave. SW, 20024
  (202) 548-4520

**ፋክስ፡-** ያተጠናቀቀውን ማመልከቻ ለDHS ESA  በ 202-671- 4400 ፋክስ ያድርጉ

## ለአልያንስ ካመለከትኩኝ በኋላ ምን ይፈጠራል?

ተቀባይነት ያገኙ ከሆኑ፣ የሚተዳደር የሕክምና ድርጅት (MCO) ጋር በዕቅድ ውስጥ እንዲመዘገቡ ይደረጋሉ። ሶስቱ MCO ዕቅዶች አምሪሔልዝ ካሪታስ (AmeriHealth Caritas)፣ ኬርፈርስት ኮሚኒቲ ሐልዝ ፕላን (CareFirst Community Health Plan)፣ እና ሜድስታር ፋሚሊ ቾይስ (MedStar Family Choice) ናቸው። **ስለ ዕቅዶቹ የበለጠ ለማወቅ፣ ወደ dchealthyfamilies.com ይሂዱ ወይም የዲሲ የቤተሰብ ደንበኛ አገልግሎትን (DC Families Customer Service)** በ **(800) 620-7802** ላይ ደውለው ያግኙ።

## አልያንስ ካላገኙም ወይም አገልግሎቴ እንዲቋረጥ ተደርጎብኛል ምን ለማድረግ እችላለሁኝ?

**እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake/።

**ይግባኝ** የመጠየቅ መብት አሎት። የእርስዎ ጥቅማጥቅሞች እንደተከለከሉ፣ እንደተቋረጡ፣ ወይም እንደተቀነሱ የሚያሳይ ማስታወቂያ በደረሰዎ **90 ቀናት ውስጥ** ይግባኝ መጠየቅ አለብዎ። ይግባኝ ለመጠየቅ ሶስት ቅደም ተከተሎች አሉ።

**ቅደም ተከተል 1፡-** የይግባኝ ቅጹን ኦንላይን https://oah.dc.gov/node/154252ላይ ያግኙ።

**ቅደም ተከተል 2፡-** የይግባኝ ቅጹን ይሙሉ።

**ቅደም ተከተል 3፡-** ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ በአንዱ ቅጹን ይሙሉ፡-

| | | |
|---|---|---|
| በዚህ ኢሜይል ይላኩት oah.filing@dc.gov። | የአስተዳደር ሰሚዎች ቢሮ (Office of Administrative Hearings)፣ 441 Fourth Street NW, Suite 450N, Washington, DC 20001 በአካል በመግኘት ያምጡት። *የቅጹን ቅጂ ያስቀምጡ።* | በግራ በኩል የሚገኘው አድራሻ ላይ በደብዳቤ ይላኩት። *የቅጹን ቅጂ ያስቀምጡ። የላኩበትን ቀን ጽፈው ያስቀምጡ። ይሄ አማራጭ አይመከርም።* |

### የእኔ ዕቅድ የምፈልገውን አገልግሎት የማይሸፍን ወይም የምፈልገውን ሐኪም የማይሰሸፍን ከሆነስ?

አሊያንሱን አንዴ ካገኙ በኋላ፣ መብቶች አለዎት። አገልግሎት ማግኘት ወይም ሐኪም ማየት ካልቻሉ፣ የእርስዎ MCO ጋር **"ቅሬታ"** ያስገቡ። ቅሬታ አንድን ችግር ላይ ያለዎትን ቅሬታ የሚገልጹበት መደበኛ መንገድ ነው። ቅሬታው ተቀባነት ካላገኘ፣ OAH ላይ **"ፍትሃዊ ክስ መሰማት"** እንዲኖር በመጠየቅ ክልከላው ላይ **ይግባኝ** ይጠይቁ (ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎች ይመልከቱ)።

*እገዛ ይፈልጋሉ?* (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ https://www.legalaiddc.org/online-intake/።